የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ–ግንቦት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 41
ADDIS ABABA - 3rd June, 1997

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፹፱ ዓ·ም·
ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፭፻፳፮

## CONTENTS

Proclamation No. 78/1997
Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation ........................ Page 526

### አዋጅ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለምአቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፪ ሚሊዮን (አሥራ ሁለት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ማርች ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፯ በካይሮ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፮ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### *PROCLAMATION NO. 78/1997*

### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA*

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 12,000,000 USD (twelve million United States Dollars) for financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project, was signed in Cairo, on the 27th day of March, 1997;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 3rd day of June, 1997;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኤኮኖሚ ልማት ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ልማት መካከል እ·ኤ·አ· ማርች ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፯ በካይሮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፪ ሚሊዮን (አሥራ ሁለት ሚሊዮን) የአሜሪካን ዶላር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፡ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation No. 78/1997."

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed in Cairo, on the 27th day of March, 1997 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 12,000,000 USD (twelve million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 3rd day of June, 1997.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of June, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE